የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በገዥው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

እስከመቼ

መጋቢት ፲፪ እስከ መጋቢት ፲፰ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
March 21 to March 27, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፲
Volume I Number 10

ዲያስፖራውና የኢትዮጵያ ነገ።

ኢትዮጵያዊያን በዓለም ዙሪያ ተበትነናል። ትክክለኛው የቆጠራ ስሌቱ ስለሌለን በዓለም ካሉት ሀገሮች በስደተኛ ብዛት፣ በስደተኛ ከሀገሩ ዕድምተኛ ንፅፅር፣ እና በተለይም በሀገሩ ውስጥና ከሀገር ውጪ ያለው የተማረው ክፍል ንፅፅር ይኼ ነው ለማለት ያስቸግረናል። ይህ ጉዳይ ግን አሳሳቢ መሆኑን ሁላችንም እንገነዘበዋለን። የዛሬዋ እስከመቼ ቁጥር ፲ ለዚህ አብይ ክስተት ትኩረት በመሥጠትና ከዚህ ሃቅ በመነሣት፤ ለነገዋ ኢትዮጵያ የዚህን በዓለም የተበተነ ኢትዮጵያዊ በነገዋ ኢትዮጵያ የሚኖረውን ሚና ትዳስሳለች።

"ይኼን ከምርጫው ምን አገናኘው?" ባዮች አትጠፉም። ጥያቄን ጥያቄ ይከተለዋልና፤ እስኪ እኛ ደግሞ ጥያቄ እናቅርብልዎ! ሀገር ሰላም ሆኖ፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዐት በሀገር ሰፍኖ፤ የሕግ የበላይነት ተከብሮ፤ ለሚያደርጉት ጥረት ተመጣጣኝ ዕድልና ውጤት የሚያገኙበት እውነታ ተከስቶ፤ ሀገርዎ ብትጠራዎ፤ አሁን ያሉበትን ይመርጣሉ? መልስዎን እንጃ፤ የእኛ መልስ ግን ቅንድብ ለማንሳትም ጊዜ አይሰጥም። በደስታ እንላለን። ለዚህም ነው በመቆርቆር ይህን ዕውነታ በመሻት የትግሉ አካል የሆንነው። ታዲያ ትግሉ ጨለምተኝነት ተላብሶት፤ ከወያኔው መለስ ዜናዊ ወይንስ ከሸዓቢያው ኢሳያስ አፍወርቂ አንዱን አምባገነን መርጦና ደግፎ፤ ሌላውን ማውገዝ መሆኑ ቀርቶ፤ ሕዝቡ ከአምባገነኑ ወያኔያዊ ሥርዓት ነፃ ለመውጣት በሚያደርገው ትንንቅ በአቸናፊነት ሲወጣ ድርሻዎ ምን ይሆናል? እንደገና ጥያቄያችንን እንመርምር! ሌሎች ሲታገሉ እርስዎ እጅዎን አጣጥፈው፤ አንድም ጥረት አካባች - ለወደፊቱ መቋቋሚያ ንዋይ፤ አለያም ነገ አለቃ ለመሆን ትምህርትዎን አሳዳጊ ነፍስ-አሳዳሪ ቀላዋጭ እንዳያደርግዎ እንፈራለን! በጄ ብለን እንቀጥል።

እርስዎ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በቅጡ የተማከለበት ሀገር ተቀማጭ በመሆንዎ፤ በሀሳብ ከርስዎ የተለየ ካላቸው ግለሰቦች ጋር፤ በስነ ሥርዓት መወያየት ለምደዋል። ድንቅ ነው። መንግሥት እንዴት የሕዝብ አገልጋይ እንደሆነ በውል ተገንዝበዋል። መልካም። ነገ እንግዲህ ይኼን በሥራ በመተግበር ሀገራችንን ሊያሠለጥኑልን ነው። ግሩም!

ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ! እስኪ ዛሬ፤ እንደርስዎ የዴሞክራሲን ምንነት ከሚያውቀው በውጭ ሀገር ነዋሪ ኢትዮጵያዊ ጋር፤ በሃሳብ ተለያይቶ በአንድነት ሆኖ በመሠረታዊው ሀገር አድን ጉዳይ አብሮ መሥራት መቻሉን ይተግብሩት።

ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ! *እስከመቼ* ከነገ በፊት ዛሬ፤ ከሞላ ጎደል በነፃና ያለተፅንዖ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት የሆነውን፤ እኔ ብቻ ልናገር እኔን ብቻ ስሙኝ ሳይሆን መደማመጥን፣ እኔ የማቀርበው መፍትሄ ብቻ ነው ትክክል ሳይሆን የሁሉንም የተለያዩ መፍትሄዎች በኩል ማመዛዘንን፤ ከያዙት አቋም የተለዬ አቋም ካላት ግለሰብ ጋር ተደማምጦ፣ ልዩነትን ተረድቶ፣ እና ሊስማሙበት በሚችሉባቸው አብሮ መሥራትን፤ እንዲያዳብሩ ትማፀንዎታለች። ለምን ይኼን እንደምንል ይረዳሉ። እያንዳንዳችን እኔ ይኼን ጠንቅቄ አውቃለሁ፤ ለኔ ይኼን ልትነግሩኝ አትችሉም ባዮች ነን። አነሣሣችን ያለምክንያት አይደለም። እስከዛሬ ድረስ ያለው የትግል ታሪካችን ያስመዘገበው ቢኖር፤ የግለሰቦች ባህርይ በትግሉ ሂደት ላይ ከፍተኛ ሚና መጫወቱን ነው። እናም እያንዳንዳችን ለዚህ መሠረታዊ የዴሞክራሲ አምድ ከተገዛን፤ ትግሉ ከግቡ ይደርሳል በተለይም የነገዋ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር የፈካ ይሆናል የሚል እምነት አለን።

የእስከመቼ ዕትም የዝግጅት ቦርድ፤
ድረስ ነጋ፣ ሕሊና ነጋሣና፣ ሀገሬ ተመቼ
eske.meche@yahoo.com